2. ተጠሪ በቀሪ የሚፈለግባትን የቤቱን ዋጋ ብር 125,000 /አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺ.ህ/ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ አለቀ ድረስ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ በመጨመር ለአመልካች ትክፈል ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 31482

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዓለምነሽ ወ/አገኘሁ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አባተ ተፈሪ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአማራ ብሄራዊ ክ/መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረብርሃን ወረዳ ከተማ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት የአፈጻጸም ክስ በደብረብረሃን ከተማ ቀበሌ 03 ክልል የሚገኘውና የቤ.ቁ. 167 የሆነውን ቤት የአፈጻጸም ተከሳሽ በብር 18,500 (አስራ ስምንት ሺ.ህ አምስት መቶ) ሸጠልኝ ቤቱንም አስረክቦኝ ነገር ግን ባለሐብትነቱን በስሜ ባለማዛወሩ ምክንያት በዚሁ ፍ/ቤት ክስ አቅርቤበት ስም እንዲያዛውር የተወሰነ ስለሆነ በዚሁ ውሳኔ መሰረት ይፈጸምልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአፈጻጸም አቤቱታውም ለአፈጻጸም ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ደርሶ በሰጡት መልስ ለአፈጻጸም ክርክሩ ምክንያት የሆነውና በሽያጭ የተላለፈው ቤት የእራሳቸው እንዳልሆነ በመግለጽ ስም ማዛወር አልችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአፈጻጸም ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለትም የወረዳው ፍ/ቤት በሽያጭ ለአፈጻጸም ከሳሹ ተላልፏል የተባለው ቤት ባለሐብትነት በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚመለከተውን አካል ጠይቆ በአፈጻጸም ተከሳሽ ስም ሳይሆን በሌላ ግለሰብ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ በመረጋገጡ የአፈጻጸም

ከሳሹ ስም ይዛወርልኝ በማለት ያቀረቡት የአፈጻጸም ማመልከቻ በአግባቡ ስላለሆነ ሊፈጸም አይችልም ብሎ በሽያጩ ጊዜ የአፈጻጸም ተከሳሹ የተቀበሉትን ብር 15,000(አሰራ አምስት ሺህ) ለአፈጻጸም ከሳሹ ሊመልሱ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአፈጻጸም ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በፍርድ አፈጻጸም ወቅት አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ መሻሩ ለሰበር ቀርቦ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ ተመርምሯል፡፡

አመልካች በደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ዳኝነት የጠየቁት ቤት ሸጠልኝ ርክክቡ የተከናወነ ቢሆንም ስም ያላዛወረልኝ ስለሆነ እንዲያዛውር ይወሰንልኝ በማለት ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ሻጩ ስም ሊያዛውሩ ይገባል በማለት ውሳኔ መስጠቱን ከመዝገቡ ለመረዳት ችለናል፡፡

በዚህ ውሳኔ መሰረት ይፈጸምልኝ በማለት የአፈጻጸም ከሳሽ/የአሁን አመልካች/ የአፈጻጸም ማመልከቻ ሲያቀርቡ አስቀድሞ ተከሳሹ ስም ሊያዛውሩ ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በይግባኝ አስካልተሻረ ድረስ ትክክል እንደሆነ የሚገመት በመሆኑ ይህንኑ ውሳኔ ከማስፈጸም በስተቀር ውሳኔውን በአፈጻጸም በመሻር ሻጩ የሽያጩን ገንዘብ ለገዢው ሊመልስ ይገባል ተብሎ ውሳኔ መስጠቱ ሙግቱ የሚመራበትን የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የሚፃረር ሆኖ ተገኝቷል፡፡



በሌላ በኩልም ለአፈጻጸም ክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ባለቤትነቱ በአፈጻጸም ተከሳሹ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ሳይሆን በሌላ 3ኛ ወገን ስም ተመዝግቦ ይግኛል ቢባል እንኳን ዋናው ክርክር ሲደረግ ይህ 3ኛ ወገን የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.41 በሚፈቅደው መሰረት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ መብቱን ማስጠበቅ የሚችል ከመሆኑም በላይ ዋናው ክርክር ሲደረግ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚችልበት ሁኔታ ካልተፈጠረም በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ መብቱን የነካ ከሆነ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 በሚፈቅደው መሰረት በሌለበት የተሰጠው ፍርድ እንዲሰረዝለት ከሚጠይቅ በስተቀር ፍ/ቤቱ በእራሱ አስተያየት ሊመለከተው አይችልም፡፡

ስለሆነም ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ጉዳዩ ይመለከተኛል የሚል 3ኛ ወገን ባልቀረበበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ በእራሱ አስተያየት በሽያጭ ለአፈጻጸም ከሳሹ ተላልፏል የተባለው ቤት በ3ኛ ወገን ስም የተመዘገበ ስለሆነ አፈጻጸሙ ሊቀጥል አይችልም በማለት የሽያጩ ገንዘብ ሊመለስላቸው ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05529/99 መጋቢት 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የሰሜን ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13181 ግንቦት 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 378/99 ግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሸረዋል፡፡
2. የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በውሳኔው መሰረት እንዲያስፈጽም ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ